## አያ - ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ!!

### (የፖለቲካ ምህዳሩን ማጥበብና መዝጋት ሊያስከትል ለሚችለው ጥፋት ተጠያቂው ይህን እያደረገ የሚገኘው የብልጽግና አገዛዝ ነው፡፡)

**ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የተሰጠ መግለጫ**
**ነሐሴ 9/12/2016 ዓ/ም**

ኢ ሕ አ ፓ ለዘመናት የቆመለት የህዝባችንን መብት ሙሉ በሙሉ ያለ አንዳንች አድርባይነትና ወላዋይነት ለማስከበር የሚያደርገውን ትግል ለመቀጠል የገባውን ቃል ኪዳን አሁንም በማደስ ትግሉን ይቀጥላል፡፡ አይንበረከክም!!!
እኛንም ሆነ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማሸማቀቅ ለህዝብ መብት መቆምንና መሟገትን ለማስቆም፣ የተቃውሞ ድምጽ ማሰማትን ፈጽሞ ለማምከን፣ ነጻ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በተለጣፊ ሀይሎች ለመተካት የሚደረገው መንግስታዊ እርምጃ ባስቸኳይ እንዲቆም፣ እንጠይቃለን ።

ኢትዮጵያ ነባርና ታሪካዊ አገር ነች። የኢትዮጵያ ህዝብም በሳል፣ ኩሩና ለነፃነቱ ቀናዔ ነው። ባዕዳን ወራሪዎችን በተደጋጋሚ አዋርዶ የመለሰው ብስለትና ጀግንነት ስላሉት ለነፃነቱ መጠበቅ አንድነቱ ማስፈለጉን ተረድቶ፣ ሁሉም ዳር እስከዳር ተጠራርቶ፣ ቀፎው እንደተነካበት ንብ በአንድነት ተምሞ ነው ነፃነትን በደሙ የዋጀልን። ህዝባችን ታጋሽና ቻይም ነው። ሁሌም የሀገርን ህልውና ለማስከበር፣ የሀገርን አንድነት ለማረጋገጥ፣ ነፃነቱንና ክብሩን ለመጠበቅ ቅድሚያን ይሰጣል። ዛሬ በጨካኝ ገዥዎች የሚደርስበትን ግፍ፣ እጅግ ዘግናኝ ጭቆና፣ አድልኦ፣ የመብት ረገጣና አይን ያወጣ ዘረኛነት እስከዛሬ የታገሰው የሀገሩን አንድነትን ሠላምን ከመሻት ነው።ግፍና ጭቆና ሲበዛበት አምርሮ በአንድነት መነሳትንም ያውቅበታል።
አረእድ አንቀጥቅጥ አብዮት አካሄዶ ለረዥም ጊዜ የቆየውን የዘውድ መንግሥትን ጥሎ፣ ያውቃል።የደርግን ወታደራዊ አምባገነን መንግሥትም የጣለው የመላው ህዝብ የተራዘመ የቡርቦራ ትግልና ተቃውሞ ጭምር ነበር፣ በኋላ እንደተባለው የህወሓት የያኔው አመራሮቹ ወታደራዊ ትግል ብቻ አልነበረም።ዛሬ ስለሀገር አንድነትና ስለ ነባር የህዝቡ የጋራ ዕሴቶችም፣ ስለ ህዝብ መሠረታዊ መብቶች መከበርም፣ ስለዜጎች የህይወት ዋስትና መረጋገጥ አስፈላጊነትም፣ ስለነፃነትና ሃሳብንና ዕምነትን ሳይሸማቀቁ ለመግለጥ ስለመቻል መናገር ያሰድባል፣ ለዛቻና ለዘለፋ ይዳርጋል፣ ያሳስራል፣ ለሰቆቃና ለግድያም ይዳርጋል። ጦርነት ህዝብን ለዕልቂት ሀገርን ለጥፋት ይዳርጋልና “እየተካሄዱ ያሉት የርስ-በርስ ጦርነቶች ይቁሙ”፣ “ሠላም ይስፈን”፣ “ያለአግባብ የታሰሩ ይፈቱ”፣ የህግ የበላይነት ይስፈን ያሉ፡ ለእስራት፣ ለእንግልት፣ ለተጓዳኝ የጤና ችግሮች ተዳርገዋል። አፈናና ዕመቃ አሁንም ያብቃ እንላለን፣ የዜጎች የህይወት ዋስትና ይከበር፣ ሃሳብን በነፃነት የመግለጥ መብት ይከበር፣ ከስፍራ ወደ ስፍራ የመንቀስቀስ መብቶች ይከበሩ፣ በገፍ የታሰሩት ሁሉ ይፈቱ ... እንላለን። ማንኛውም ህገመንግሥት የሚወጣው ገዥዎች በፈለጉ ጊዜ አንቀጾችን እየመዘዙ “ህግ እናስከብራለን” እንዲሉ ለማስቻል ብቻ ሳይሆን እነሱንም ጭምር በህግ የበላይነት ሥር እንዲመሩ፣ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ፣ ተጠያቂም እንዲሆኑ ለማድረግ ጭምር ነው። አሁንም የዳኞች ነፃነት ይጠበቅ፣ የህግ የበላይነቱ በሙሉ ትርጉሙ ይከበር እንላለን። በአንድ ሀገር ውስጥ የህግ የበላይነት ከሌለ ገዥዎች

ሠላምና መረጋጋትን ለማምጣት የሚሞክሩት በሃይልና በጉልበት ነው ማለት ነው።ህግና ስነሥር ዓትን ረዘም ላለ ጊዜ በአፈናና ዕመቃ ለማስፈን መሞከር ደግሞ የለየለት አምባገነናዊነት ነው።የኢትዮጵያ ህዝብ አምባገነናዊነትን ለረዥም ጊዜ ሊሸከም አይችልም፣ አይገባምም እንላለን።
ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከሚስተዋለው የዜጎች የህይወት ዋስትና እጦት፣ በነጻነት በሀገራቸው ዉስጥ ለመንቀሳቀስ አለመቻል፣ ዜጎች በየመንገዱ እየታፈኑ መታገት፣ ታጋቾችን ለመፍታት ከፍተኛ ክፍያ መንግሥት በሚቆጣጠረው ባንክ በኩል ለመክፈል መገደድ፣ ህዝብን ከመኖሪያ በዘፈቀደ ማፈናቀል፣ የዜጎችን መኖሪያ ቤትና ንብረት በመከላከያ ሃይል መድፍና መትረየስ ማውደም፣ ሠላማዊ ዜጎችን ህይወት በመታደግ ፈንታ በዘር ፈርጆ ለእ ስራትና ለእንግልት ለግድያም መዳረግ፣ ... ከፍተኛ ግፍና በደል ነው። ይህ ሁሉ በዜጎች ላይ የሚፈጸም ግፍና ሰቆቃ እንዲቆምና ፈጻሚዎችም ለፍርድ እንዲቀርቡ መደርግ አለበት።
ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲፈጠር ነው የምንፈልገው።ብልጽግና ፓርቲም ቃል ይገባ የነበረው ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የማሸጋገሩን ተግባር አከናውናለሁ ብሎ ነበር። ታዲያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማለት እኮ ሰብዓዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች መከበርን፣ ሃሳብን በነፃነትን የመግለጥ መብትን፣ የአያሌ ፖለቲካ ፓርቲዎች መኖርንና በነፃነት መንቀሳቀስን የሚጨምር የመሰባሰብና የመደራጀት መብትን፣ ነፃና ርትዓዊ ምርጫ መካሄድን፣ የህግ የበላይነት መስፈንን ማለትም የፍትኅ ሥርዓቱ ያለጣልቃ-ገብነት መሥራትን፣ የህግ-አውጭና የአስፈጻሚው አካል መለያየትና መከባበርን፣ያካትታል። እነዚህን አለማሟልት ማስወቀሱ እኮ አግባብ አለው።አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በሆነ ምርጫ ወቅት ሥልጣን ጨበጠ ማለት እድሜልኩን እንዳሻው ያባዝት ማለት አይደለምና፣ዛሬም ነገም የህዝቡን ነፃነትና መብት እንድታከብሩ ትጠየቃላችሁ።
የፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት የመንቀሳቀሳቸው አስፈላጊነት ለቆሙለት ህዝብ መብት፣ ነፃነትና ጥቅሞች መከበር ለመሟገት እንዲችሉ ጭምር ነው። በሀገራቸው ዜጎች ላይ የሚፈጸም በደልንና ጎጅ ተግባርን ለይቶ በማቅረብ ገዥውን ሃይል ሃላፊነቱን እንዲወጣ በሠላማዊ መንገድ መጠየቅና፣ ግፍና በደል ከፈጸመም ተጠያቂ ማድረግ፣ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጠበቅ ነው። በስልጣን ላይ የሚገኙ ገዥዎችም  የህዝብን ፍላጎት  እንዲሁም የሀገርን ደህንነት  የሚያስጠብቅ ፖሊሲ ከሌላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች አማራጫቸውን አቅርበው ሊሞግቷቸው ቢገባም፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈለገው ተቃዋሚ ነኝ እያለ ለገዥዎች ውዳሴን የሚያቀርብ እንዲሆን፣ ገዥዎች ፍርፋሪ እንዲወረውሩለትና በዚያ ረክቶ እንዲኖር ነው። ይህ አስነዋሪ ተግባርና በሀገራችን አምባገነናዊነት እንዲሰፍን መተባበር እንጂ ተቃዋሚ ሆኖ የህዝብን ብሶት ማስተጋባት፣ የህዝብን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ በሠላማዊ መንገድ መታገል ሊባል አይችልም እንላለን።
የፖለቲካ ፓርቲዎች ህዝብና ሀገርን  በሚመለከት ጉዳዮች ላይ ማህበረስቡ ንቁ ተሳትፎ ሊያደርግ የሚያስችለውን የማንቃት  እና የማደራጀት   ተግባር ላይ  ሳይታክቱ መስራትን ይጨምራል፡፡ ህዝብ ተደራጅቶ  ለመብቱ እንዲቆም፣ ጥቅሙን እንዲያስጠብቅ ማስታወስ፣ ማስረዳት፣ መቀስቀስ፣ በተለይ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተግባር ሊሆን ይገባል።ህዝብን በሁሉም መልኩ ማብቃት  የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱ መሰረታዊ  ተግባርና ተል ዕኮአቸውም መሆኑ ለአፍታም ሊዘነጋ ባልተገባም ነበር፡፡ ፓርቲያችን ኢሕአፓ ከተመሰረተበት ከ50 አመት በፊት  ጀምሮ  እነዚህን  መተክሎችን መሰረት አድርጎ ለተግባራዊነቱም መታገሉን ቀጥሏል፡፡ ይህንንም በማድረጉ በደርግ ግድያና ሰቆቃ ተፈጸመበት። በህወሓት/ኢሕአዴግ ወገዛው፣ እመቃው፣ደብዛውን የማጥፋት ሥራው ቀጠለ።አሁን ደግሞ እንደገና በህጋዊነት ለመንቀሳቀስ ሲሞክር፣ብልጽግና በተራው ይቆራቆሰው ጀመር። ከተራ የስም ማጥፋት  እስከ አሰቃቂ እስራት   ግፍ  ተፈጽሞበታል፡፡አባላቱን ማስፈራራት፣ ማሳደድ፣ለፈስፈስ ካሉም ማስኮብለል፣ ጠንከር ያሉትን ለማንበርከክ መሞከር ሥራዬ ብሎ ቀጥሎበታል። ኢሕ አፓ በፊትም አባላቱ ላመኑበት ሲፋለሙ ነው የኖሩትና ሁሉንም ዐይነት መስዋዕት የከፈሉት። ዛሬም አባላቱ ያንኑ ለህዝብና ለሀገር በሙሉ ታማኝነት የመቆምን ክቡር ዓላማ እንዳነገቡ ናቸውና እመቃና ማስፈራራት ወይንም ቡርቦራ

ከኢሕአፓነት ከፍታ አያዋርዳቸውም። ዕውቁት። ፍንከች ሳይል ለፍትህ ለነጻነት ለዕኩልነትና ለአንድነት እነሆ ትግሉን እንደቀጠለ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ሰአት ድርጅታችን በሰላማዊ መንገድ መታገልን፣ መርጦና አምኖበትም ነው በህጋዊነት ተመዝግቦ የፖለቲካ ትግል ለማድረግ እየሞከረ ያለው። እንደተቃዋሚ ፓርቲ ለመታገል የሚያስችለው ሁኔታ ተሟጧል ብሎ እስከሚያምን አሁን እንደሚያደርገው የፖለቲካ ትግሉንና የማደራጀት ሥራውን አጠናክሮ ይቀጥላል። በህጋዊነትና በሠላማዊ መንገድ የመታገያውን ድባብ ብልጽግና በየቀኑ እያጠበበው እየመጣ ቢሆንም ሁኔታውዎች የፈቀዱለትን ያህል ለማድረግ ይጥራል። ነገር ግን፣ እንዳለፉት አገዛዞች ሁሉ ዛሬም ብልጽግና የጸጥታ ሃይሉን በመጠቀም፣ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ጫና እያደረገበት ይገኛል፡፡

ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል በዚህ አመት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ውስጥ እየተካሄዱ ያሉትን ጦርነቶች፣ በህዝብና ሀገር ላይ የሚያደርሱትን ጉዳትና ውድመት በመረዳት፣ “ጦርነት ይብቃ” በሚል መርህ ህዝብ ድምጹን እንዲያሰማና ሰላምን እውን ለማድረግ ተጽዕኖ እንዲያደርግ ከሌሎች ፖለቲከኞች ጋር በመሆን የጠራውን ሰላማዊ ሰልፍ ገዥዎች በክልከላና በእስራት ማስቆማቸው ሳይበቃቸው፣ “እንዴት ሳንፈቅድላችሁ ይህን አሰባችሁ” በሚል ትዕቢት፣ የድርጅታችንን አባላት ማስፈራራት፣ ከዚያም አልፎ የድርጅታችንን ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር እና የፓርቲያችንን ዋና ሊቀመንበር እና የሰልፉ አስተባባሪዎች የነበሩትን ዐዋሽ አርባ ወደሚባል ማጎሪያ ወስደው ከቤተሰብ፣ከዘመድ-አዝማድ፣ ከጠበቃ፣ ከሐይማኖት አባት፣ አርቀው አስረው አሰቃይተዋቸዋል። ለምን በሠላማዊ መንገድ የሚታገል ፖለቲከኛ እንደዚህ ይንገላታል።ሃሳብን በነጻነት የመግለጥ መብት እኮ ነው ሠላማዊ ሠልፍ ማድረግ!!
፡፡ይህ አፈና ካልሆነ ምን ሊባል ነው?!

በቤነሻንጉል የሚገኙትን የድርጅታችን፣ አመራር ያለአግባብ፣አስረው። እስከ አለፈው ሳምንት እንግልትና ስነልቦናዊ ጉዳት አድርሰውባቸዋል፡፡የዜጎች ሙሉ መብቶችና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት የመንቀሳቀስ መብት እየተረገጠና እየተጨፈለቀም ነው።

በተለያዩ ጊዚዎች ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ባደረጉት ስብሰባዎች የድርጅታችንን ስም በማንሳት “ አንድ ቦታ የተቸነከረ፣ ወዘተ” የሚል ጸያፍ ስድብ ሰድበውናል። በተደጋጋሚ ፓርቲውን ሲያብጠለጥሉ ህዝብ የተመለከተውና የታዘበው ሀቅ ነው ።

አሁን ለምን ብልጽግና በኢሕአፓ ላይ ትንኮሳ አበዛ? ማንኛውም አምባገነን ሥርዓት ሁሉም ጸጥና ረጭ ብሎ እንዲገዛላቸው ነው የሚፈልጉት። በቅርቡ የድርጅታችን ማእከላዊ ኮሚቴ ባካሄደው ጉባኤ ሰፊ ውይይት አካሂዶ ሀላፊነት በተሞላው ሁኔታ በሀገራችን ውስጥ የተጀመረው የብሔራዊ ምክክር ከምስረታው ጀምሮ የነበሩትን ድክመቶች፣ እየተጓዘበት የሚገኘው መንገድና ሂደቱን በመመርመር፣ የሚታዩበትን ህጸጾች ነቅሶ በማውጣት ውጤታማ ምክክርን እውን ለማድረግም መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች በጥናት ላይ የተመረኮዘ የፖሊሲ አማራጭ በይፋ መግለጫ ካሳወቀ ወዲህ በተለይ በድርጅታችን ላይ የሚካሄደው ጫናና ማዋከብ እጅግ ተጠናክሯል፡፡

በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የድርጅታችንን መሪዎችና አባላት የማስፈራራት፣ የስድብ ናዳና ዛቻዎችን የማድረግ፣ ከድርጅት ሀላፊነትና ከድርጅታቸው አባልነት እንዲለቁ ጫና ማድረግ፣ አንዳንድ ሆድ-አደር ግለሰቦችን በመጠቀም ለማስኮብለል መሞከር፣ የተለያየ ማስጠንቀቂያዎችን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ለአባሎቻችን እንዲደርሱ ማድረግ፣ ቀጥሏል፡፡

አሁን የሚታየው ማስፈራራትና ተመሳሳይ ተግባሮች እጅግ በተቀነባበረ ሁኔታ በተለይም ተጽዕኖ ፈጣሪ ናቸው ብለው በሚገምቷቸው የፓርቲያችን መሪዎችና አባላት ላይ አነጣጥሮ ቀጥሏል፡፡

ይህ ሁሉ የመደራጀትና ሀሳብን በነጻና በሰላማዊ መንገድ የመግለጥ መሰረታዊ መብትን የሚጻረር ብቻ ሳይሆን ነጻና ሞጋች የፖለቲካ ድርጅቶችን ሊያሰራ የሚችል ሰላማዊ መድረክን እጅግ የሚያጠብ አልፎ ተርፎም ሙሉ በሙሉ የሚዘጋ እርምጃ ነው፡፡

ድርጅታችን ኢ ሕ አ ፓ ቀደም ባሉ አገዛዞች ተገፍቶና ተገዶ በህጋዊና ሰላማዊ የትግል መድረክ እንዳይንቀሳቀስ ታግዶ እንደቆየ ታሪክ የሚዘክረው ነው፡፡አሁንም ገዥው አካል የሚያካሂድበት ወከባና

Phone :+251 911400982 Email:eprp@eprp-ihapa.com

ተጽእኖ ተገቢነት የሌለው ከህዝባችንና ከፓርቲያችን አባላት እንዲሁም ከደጋፊዎቻችን ፍላጎት ጋር የሚጻረር መሆኑን ደግመን ደጋግመን ልናነሳ እንወዳለን። ሠላማዊ የፖለቲካ መድረኮችን መዝጋት ለማንም አይበጅም።ከደርግ ተማሩ እንጂ!!

በሀገራችን ውስጥ እየተካሄደ የሚገኘው በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ሰፊ ጦርነት ተወግዶ ሁሉም ሀይሎች ሰላማዊ በሆነ መድረክ ሀሳባቸውን የሚገልጡበት፣ ልዩነቶቻቸውን በሰላም የሚፈቱበት ድባብ እንዲፈጠር እኛም ሆንን ህዝባችንና አለም አቀፍ ማህበረሰቡም በሚወተውትበት በአሁኑ ሰአት ድርጅታችንን ከሰላማዊ መድረኩ ለማስወጣት ብልጽግና የሚያደረግብን ተጽእኖ ማዋከብ፣ ማስፈራራት ወዘተ ማንንም የማይጠቅም፣ እንዲያውም ሁሉንም የሚጎዳና ሀላፊነት የጎደለውም ነው እንላለን፡፡ ምክራችን፣ ተዉን፣ አትግፉን የሚል ነው።

በዚህ ምክንያት ለሚደርስ ጥፋት ተጠያቂው የሚሆነው የሰላማዊ ትግል መድረክን ከማጥበብ አልፎ፣ እያኮራመተው፣ ከዚያም አልፎ እየዘጋው የሚገኘው የብልጽግና ፓርቲና የሚመራው መንግስት እንደሆነ ህዝባችን፣ ሁሉም የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች እንዲሁም አለም አቀፉ ህብረተሰብ እንዲገነዘብ ከወዲሁ እንገልጻለን፡፡

ሉም ኢትዮጰያዊ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች እንዲሁም የሲቪክ ማህበራት ድምጻቸውን በጋራ እንዲያሰሙ አስቸኳይ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

ኢ. ሕ አ ፓ የህዝባችን ሰቆቃ የሚያከትምበት፣ ሁሉም ዜጋ የነፃነት ዐየር የሚተነፍስበት፣ የተሻለ ነገን እውን ለማድረግ የሚያደርገውን ሀቀኛ ትግል ይቀጥላል።

ድል ለኢትዮጰያ ህዝብ!

ነፃነት በቀጣይ ትግልና መስዋዕት ገና ያብባል!!

ነሐሴ 9/12/2016 ዓ/ም
አዲስ አበባ